# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ.ቁ 253740

ህዳር 27 ቀን 2016ዓ/ም

ዳኞች ፡- ብርሃኑ አመነው

በእውቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

አመልካች ፡- አብረሃም ይሳቅ

ተጠሪዎች ፡- ፍትህ ሚ/ር ዐቃቤ ህግ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ፡፡

መዝገቡ ለዚህ ችሎት የቀረበው አመልካቹ በዋስ ለመፈታት ያቀረበውን ጥያቄ ባለመቀበል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 232763 ላይ በቀን 25/12/2015 ዓ/ም የሰጠውን ብይን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማጽናት በመ.ቁ. 012961 በቀን 18//01/2016 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ በሚል በሰበር ችሎት እንዲታረም አመልካቹ ባቀረበው አቤቱታ መነሻ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ሲታይ በስር ፍርድ ቤት አቃቤ ህግ በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ አመልካቹ የወንጀል ህግ አንቀጽ 626(1) ተላልፎ እድሜዋ 15 ዓመት ከሆናት የግል ተበዳይ ጋር ግብረ ስጋ ግንኙነት ፈጽሟል፡፡ በሚል የተከሰሰ ሲሆን ክሱ ሊሰማ ቀጠሮ በመሰጠቱ አምላካች በዋስ እንዲፈታ አመልካቹ ጠበቃ ባቀረቡት ጥያቄ ላይ አቃቢ ህግ በሰጠው አስተያየት አመልካቹ የተከሰሰበት ድንጋጌ እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ አመልካቹ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ቅጣቱን በመፍራት ዋስትና ግዴታ አክብሮ ላይቀርብ ይችላል በሚል የተቃወመ ሲሆን ፍርድ ቤቱም አመልካቹ ጥፋተኛ የሚባል ከሆነ ቅጣቱን አመዛዝኖ ላይቀርብ ይችላል የሚል ግምት በመያዝ የዋስትና ጥያቄውን በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 67/ሀ/ መሰረት ባለመቀበል በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራቀኙን ሰምቶ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተገቢ ነው በሚል አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ሲሆን የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ ሲታይ የስር ፍርድ ቤት ቀጠሮ አክብሮ ላይቀርብ ይችላል በሚል የወሰደው ግምት የዋስትና መብት ሊከለከልባቸው የሚችሉባቸው ተጨባጭ መንደርደሪያና መረጃ እና በቂና ህጋዊ ምክንያት በሌለበት የተወሰደ ግምት በመሆኑ ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ 131863 ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ያላገናዘበ ነው በማለት በሰበር እንዲታረም ጠይቋል፡፡ የአመልካቹ አቤቱታ ተመርምሮ የአመልካቹ የዋስትና ጥያቄ በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ የተደረገበትን አግባብነት ከህገመንግስት አንቀጽ 17/1/ እና 19/6/ እንዲሁም ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ 131863 እና ሌሎች መዝገቦች ላይ ከሰጠው የህግ ትርጉም ጋር አገናዝቦ ለመመርመር ጭብጥ ተይዞ አቃቤ ህግ መልስ እንዲሰጥ አዟል፡፡ አቃቤ ህግ በቀን 12/03/2016 ዓ/ም ጽፎ ባቀረበው መልስ አቃቤ ህግ የዋስትና ጥያቄ የተቃወመው ከተፈጸመው የወንጀል ድርጊት፣ከወንጀሉ ክብደትና አፈጻጸም አንጻር መሆኑን፣ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ 67874 እና ሌሎች መዝገቦች ላይ በሰጠው ውሳኔ የወንጀሉ ክብደትና አፈጻጸሙ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 67/ሀ/ መሰረት ዋስትና ለመከልከል ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ስለተወሰነ በዚህም ጉዳይ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የህግ ስህተት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ክርክር በአጭሩ ከላይ የተገለጸውን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነው አመልካቹ ዋስትና ጥያቄ ውድቅ የተደረገው የሚጣልበትን ቅጣት በመፍራት ቀጠሮ አክብሮ ላይቀርብ ይችላል የሚል ግምት በመውሰድ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ይዘት ያሳያል፡፡ የአመልካቹ መከራከሪያም ፍርድ ቤቱ ይህንን ግምት ለመውሰድ ተጨባጭ መንደርደሪያም ወይም መረጃም ሆነ ህጋዊ ምክንያት የለውም የሚል ነው፡፡

በመሠረቱ በወንጀል የተከሰሰ ሰው በዋስትና ወረቀት ተለቆ ክርክሩን የመከታተል መብት መሠረታዊ ህገ መንግስታዊ መብት ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 19(6) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ የዚህ ጽንስ ሃሳብ መሠረቱ በወንጀል የተከሰሰ ሰው ጥፋተኝነቱ በፍርድ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

እስከሚረጋገጥ ድረስ ንፁሁ ሆኖ የመገመት መብት አለው ከሚለው የህግ ግምት የሚመነጭ ነው፡፡ የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 20(3) ድንጋጌ ይዘትም ይህንኑ ሃሳብ ያመለክታል፡፡ ይሁንና ህግ አውጭው አካል በልዩ ሁኔታ በግልፅ በህግ ሲደነገግ ወይም ህጉ ለፍርድ ቤት በሰጠው ስልጣን መነሻ ፍርድ ቤቶች የቀረቡላቸውን ምክንያቶች በማመዛዘን ዋስትና መብቱን ሊከለክሉ የሚችሉበት ሁኔታዎች አሉ፡፡ ስለዚህም በህግ በልዩ ሁኔታ ካልተከለከለ በዋስትና መቆየት መሠረታዊ ህገመንግስታዊ መብት ሲሆን ክልከላ የሚደረገው በልዩ ሁኔታ መሆኑን የድንጋጌው ይዘት ያሳያል፡፡ የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 19(6) እንዲሁም የወ/መ/ሥ/ሥ/ህግ አንቀጽ 63 እና 67 ጣምራ ንባብ ይህንኑ የሚያስገነዝበው፡፡ በህግ የተመለከቱ ልዩ ሁኔታዎች ደግሞ በጥንቃቄ እና በጠባቡ መተርጎምና ተግባራዊ መደረግ እንዳለበት ህግ አተረጓጎም መርህ ያስገነዝባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካቹ የተከሰሰበት የወንጀል አንቀጽ 626(1) እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ቢሆንም በመርህ ደረጃ ዋስትና የሚያስከለክል አይደለም፡፡ የወ/መ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 63 ይመለከታል፡፡ሆኖም በወ/መ/ሥ/ሥ/ህግ አንቀጽ 67 ስር የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ምክንያቶች መኖራቸው ሲረጋገጥ የዋስትና መብቱ በፍርድ ሊነፈግ እንደሚችል እሙን ነው፡፡ በዚህም ጉዳይ ዐቃቤ ህግ ዋስትና ለመቃወም ያቀረበው ምክንያት አመልካቹ ላይ ሊወሰን የሚችለው ቅጣት ከባድ በመሆኑ ቅጣቱን በመፍራት ቀጠሮ አክብሮ ላይቀርብ ይችላል የሚል ሲሆን ፍርድ ቤቱም ይህንኑ ምክንያት የተቀበለ መሆኑን የውሳኔው ይዘት ያሳያል፡፡ ዋስትና መብቱን ለመንፈግ ፍርድ ቤቱ የጠቀሰው የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ67(ሀ) ድንጋጌን ነው፡፡ በዋስትና ወረቀት የመለቀቅ ጥያቄ ተቀባይነት ከሚያጣባቸው ምክንያቶች አንዱ አመልካቹ በዋስትና ወረቀት የተመለከቱትን ግዴታዎች የሚፈጽም የማይመስል የሆነ እንደሆነ ስለመሆኑ በአንቀጽ 67(ሀ) ስር ተደንግጓል፡፡ ፍርድ ቤቶች በዚህ ምክንያት ዋስትና መከልከል የሚችሉበት ምክንያት በህጉ ላይ በግልጽ አልተመለከተም፡፡ ይሁንና ድንጋጌው ፈቃጅ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ከድምዳሜ ሊደርስ የሚችለው በዘፈቀደ ሳይሆን በቂ ምክንያትና መረጃ ላይ ተመስርቶ መሆን እንዳለበት ሰበር ችሎቱ ገዥ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡ (ሰበር መ/ቁ67874 ቅጽ 13፣ መ/ቁ131863 እና 134228 ቅጽ 20 ላይ ታተመውን ይመለከታል)፡፡

በዚህ ጉደይ ፍርድ ቤቱ ዋስትና ጥያቄውን ውድቅ ያደረገው የሚጣልበትን ቅጣት ፈርቶ በቀጠሮ ላይቀርብ ይችላል የሚል ግምት በመያዝ እንጂ ሌላ ምክንያት ስለመኖሩ የጠቀሰው ነገር የለም፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ቅጣትን መፍራት የአመልካቹ ብቻ የተለየ ባህርይ ነው  በማለት የሚያስችል በቂ መነሻ የለም፡፡ ይህም ቢሆን የዋስትና ግዴታውን ያከብድ እንደሆን እንጂ ዋስ መብቱን ለመንፈግ በቂ ምክንያት አይደለም፡፡ ስለዚህም ግዴታውን አክብሮ አይቀርብም ለማለት የሚያስችል ሌላ በቂ ምክንያት በሌለበት ቅጣቱ ከባድ ነው በሚል መነሻ ብቻ ዋስትና መንፈጉ ተገቢነት የለውም፡፡ ከዚህ አኳያ የስር ፍርድ ቤት እንዲህ አይነት ግምት ለመውሰድ በቂ መንደርደሪያ መኖሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ እና ሰበር ችሎቱ የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ያላገናዘበ በመሆኑ ሰበር ችሎቱን ገዥ ውሳኔ የሚቃረን ሆኖ  አግኝተናል፡፡ በዚህ አግባብ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሸ) እና 10(1/ሀ) መሰረት በማረም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1ኛ የአመልካቹን በዋስ የመፈታት መብት ውድቅ በማድረግ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 232763 ላይ በቀን 25/12/2015ዓ.ም  የተሰጠው ብይን እና ይህንኑ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ012961 ላይ በቀን 18/01/2016ዓ.ም  የሰጠው ውሳኔ በሰበር ስነ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1/ለ) መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ አመልካቹ በዋስትና ወረቀት ተለቆ ክርክሩን የመከታተል መብት አለው ብለናል፡፡

3ኛ የዋስትና ግዴታ ዐይነትና መጠን በሚመለከት ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን አስተያየት ተቀብሎ እንዲወሰን ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መልሰናል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ም

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !